# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 45 መጋቢት 17 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

**‹‹የሞቱትን ማወቅ ለስራችሁ የሚያስፈልጋችሁ አይደለም። እኔም ብሆን ለእናንተ የመንገር ግዴታ የለብኝም››**

**አንባቢያችን ከ አዲስ አበባ**

**ገጽ 3 ላይ ይመልከቱ**

## ሂውመን ራይትስ ዋች ወያኔ በጸረ-ሽብርተኝነት ስም ሊያወጣው እየተሰናዳ ያለውን አዋጅ አጥብቆ ኮነነ

ታዋቂው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሂውማን ራይትስ ዎች መጋቢት 30 ቀን በወያኔ የጸረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅ ላይ ትንታኔ አቅርቧል። በትንታኔው ይህ ረቂቅ ህግ ግልጽ ባልሆነና ሰፊ ትርጉም ሊኖረው በሚችል ሁኔታ አሸባሪነትን በመተርጎሙ መንግስት በዓለም አቀፍ ህጎች የተጠበቁ የግለሰብ መብቶችን እንዲጥስ መንገድ እንደሚከፍትለት ገልጿል። ከዚህ አተረጓጎም የተነሳም አዋጁ መንግስት የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን የሚያሳድድበት መሳሪያ ሊሆን

እንደሚችል ያለውን ስጋት በግልጽ አስቀምጦአል።

እንደ ሂውማን ራይትስ ዎች ግምገማ ይህ አዋጅ ካለፈ ሰላማዊ ሰልፎች እና በግልጽ በመንግስት ላይ የሚደረጉ ማንኛውም ዓይነት የሰላ ሂሶች የአሸባሪነት ስራ እየተባሉ ሊታገዱ እንደሚችሉና ከዚህ ጋር በተያያዘ አጥፊ ተብለው የሚፈረጁ የመንግሥት ተቀናቃኞች ፣ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ለትርጉም በማያስቸግር አነጋገር አሸባሪ ተብለው ሊወነጀሉና ለረዥም ጊዜ እስራት ወይም የሞት ቅጣት ሊዳረጉ እንደሚችሉ ይፋ አድርጎአል።

ለምሳሌ፥ በመንግሥት ላይ ያለውን ተቃውሞ ለመግለጽ የሥራ የማቆም አድማ በማድረግ የህዝብ አገልግሎት እንዲያቋረጠ ያደረገ ሳይቀር የሽብርተኝነትን ወንጀል እንደፈጸመ እና ከ15 ዓመት እስከ ሞት በሚደርስ ቅጣት እንደሚቀጣ ረቂቅ አዋጁ የሚደነግግ ስለሆነ ፤ ይህ ረቂቅ ህግ የዜጎችን ተቃዉሞአቸውን በሰላማዊ መንገድ የመግለጽ መብት ሁሉ የሚጋፋና ፍጹም አምባገነናዊ ድንጋጌ እንደሆነ ገልጾ አንዲህ አይነቱ ህግ ሆን ተብሎ ዜጎችን ለማፈን የሚወጣ እንደሆነ ገልጿል። ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ ዜጎች ብሶታቸውንና ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ ይዘውት የሚወጡት መፈክሮች ሳይቀር መንግሥትን ካላስደሰተ "የሽብር ወንጀል ለመፈጸሚያ የሚጠቅም ንብረት ይዞ ተገኘ" ተብሎ ሊያስወነጅልና በጥፋተኝነት ሊያስፈርድ አንደሚችል የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቱ ባወጣው መግለጫ አስታውቆአል።

ከዚህም በተጨማሪ ረቂቅ ህጉ "ሽብርተኛነትን" ይረዳሉ ተብለው የሚታሰቡ ጽሁፎችን እና ንግግሮችን የሚያደርጉ ሰዎችን የሚወነጅል ሲሆን፤ ይህም ቀድሞዉኑ በወያኔ የጥቃት በትር ስር እየተንገዳገዱ ያሉትን ጥቂቶቹን የነጻው ፕሬስ አባላት ጨርሶ የማጥፊያ ጥንስስ ሳይሆን አይቀርም ሲል የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ ስጋቱን ገልጿል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በበረከት ስምኦን በለንደን በድብቅ የጠራው ስብሰባ ተበጠበጠ

ሀሙስ መጋቢት 10፣ 2001 በንጹሀን ደም እጁ በተጨማለቀው በበረከት ስምኦን ሰብሳቢነት በለንደን የሚገኘው የወያኔ ኤንባሲ ለወያኔ ደጋፊዎች በድብቅ የጠራው ስብሰባ ከ ኢትዮጵያዊያን በደረሠበት ከፍተኛ ተቃውሞ ሊካሄድ እንዳልቻለና እንደተበተነ በስፍራው የተገኘው የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ ካስተላለፈልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

# ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## 'ዘ-ኢኮኖሚስት' የተሰኘው ጋዜጣ አዘጋጅ በአዲስ አበባ ያዘጋጀውን ስብሰባ በድንገት መሰረዙ ተገለጸ

መቀመጫውን ለንደን ያደረገው እና ከ162 ዓመት በፊት የተመሰረተው ታዋቂው ጋዜጣ በተለያዩ አገሮች ተመሳሳይ ዝግጅቶችን ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ግን ይህ የመጀመሪያው የተገለጸ ሲሆን ውይይቱ ሊካሄድ ታስቦ የነበረው እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ማክሰኞ ከማርች 23--24 በአዲስ አበባ ሸራተን ሆቴል እንደነበር ታውቋል።

ስብሰባው ሊደረግ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት፥ እነመለስ በስበሳው ላይ አልካፈልም በማለታቸው ስብሰባው መሰረዙን የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ገልጸዋል። ወያኔ በስብሰባው ላይ አልካፈልም ያለበት ምክንያትም አስተባባሪዎቹ ለስብሰባው ካዘጋጁቸው ጽሁፎች ውስጥ ባንዱ ላይ ባለመስማማቱ እንደሆነም ተገልጿል። ጋዜጣው የጽሁፉን ይዘት እስካሁን ባይገልጸውም፣ ወያኔ መራሹን ኢኮኖሚ የሚተች ሊሆን እንደሚችል ታዛቢዎች ግምታቸውን ሰጥተዋል።

ዳግማዊ በድህረ-ገጹ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ባወጣው ትንተና፣ ዘ ኢኮኖሚስት ስለስብሰባው ማብራሪያ በሰጠባቸው ጽሁፎች ላይ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ እና ተጨባጭ እውነታ ላይ መመስረት የሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች በዋናነት የሚብብ መሰረዝ ስለመለስ ምን ያመለክታል በሚል ትንታኔውን ያቀረበው ዳግማዊ፥ መለስ ይሄንን ስብሰባ ለማካሄድ ሲስማማ ጋዜጣው ነፃና ገለልተኛ መሆኑን ዘንግቶት እንዳልሆነ ጠቅሶ፣ ስብሰባው ጥቂት ቀናት ሲቀሩት መሰረዙ ግን ተቋሙ ስብሰባውን ለማዘጋጀት እስካሁን ላወጣው ወጪ ሲል መለስ ያልወደደዉን ጽሁፍ አስወግዶ ስብሰባውን ይቀጥላል ብሎ ተማምኖ እንደሚሆን ግምቱን ሰጥቷል። አምባገነኑ መለስ ቃል እየገባ ማፍረስ የለመደው ተግባር መሆኑን የፃፈው ዳግማዊ፣ ምናልባት የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ቃሉን አክባሪ እና የተከበረ ሰው እንደሆነ ገምተው ሳይሳሳቱ እንዳልቀረ ገልጿል።

"ከዚህ የተገኘ ጥሩ ነገር ቢኖር የመለስ ዝቃጭ ባህሪ፣ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት ሲሄድባቸው የነበሩትን ርቀቶች ዛሬም እንደቀጠለበትና ኢ-ታአማኒ የሆነ የመደራደሪያ ስልቱ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ለአለም ህዝብ በይፋ ሊዘገብበት መሆኑ ነው፤" በማለትም ትንታኔውን ደምድሟል።

## ከመጠን ያለፈ የብድር ብዛት ለኢኮኖሚው ውድቀት ምክንያት መሆኑ ተገለጸ

የእንግሊዙ የዓለምአቀፍ ልማት ዲፓርትመት ዋና ኢኮኖሚስት ፕሮፌሰር አለን ዊንተርስ አለማቀፉ የኢኮኖሚ ቀውስ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ እያደረሰ ያለውን ተጽእኖ ለመገምገም ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ የተለያዩ የዜና አውታሮች መግለጻቸው ያሚታወቅ ነው። ፕሮፌሰሩ የወያኔ ባለስልጣናትን አግኝተው ያነጋገሩ መሆን ያታወቀ ሲሆን ከስብሰባው በኋላ በሰጡት አስተያየት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አሁን ያለበት ችግር ውስጥ የገባው ከባንኮች ከመጠን ያለፈ ብድር በመውሰዱ እና ያም ባስከተለው የዋጋ ግሽበት ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

ወያኔ በምርጫ 97 ማግስት ህግ ከሚፈቅድለት እጅግ የላቀ ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ መበደሩ ይታወሳል። በምርጫው የደረሰበትን ሽንፈት ለመደበቅ ሲል የአገሪቱን የረዥም ጊዜ ጥቅም ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ሲንቀሳቀስ የነበረው አገዛዝ፣ አገሪቱ የሌላትን ገንዘብ እያሳተመ በገበያው ላይ ሲገለብጥ መክረሙ ይታወቃል። ዋና ዋና ባለስልጣኖቹ ወደ ኪሳቸው ከሚያስገቡትና ወደ ውጭ አገር ከሚያሸሹት በተጨማሪ፣ አገዛዙ ደጋፊ በገንዘብ የሚገዛ መስሎት ቁጥሩ የማይታወቅ የአገሪቱን ሃብት በአገሪቱ ዙሪያ ላሉ ካድሬዎች እና ለሌሎች እያርከፈከፈ ማባከኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ቀሪውን ደግሞ የመንግስት ባንኮች ጉቦ ለከፈላቸው እና ለገዢው ፓርቲ ቅርብ ለሆነ ሁሉ የንግዱን ፍሬ ነገር ሳይመለከቱ ሲያበድሩ መክረማቸው ይታወሳል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በአፍሪካ ዝርፊያው ተባብሶ መቀጠሉ ተገለጸ

ባለፉት ጥቂት አመታት ድሀ ከሚባሉ አገሮች ወደ እንግሊዝ ባንኮች ብቻ የተላለፈው የገንዘብ መጠን እጅግ እየናረ እንደመጣና ባለፈው አመት ብቻ ከድሀ አገሮች ወደ ሀብታም አገር ባንኮች የተላለፈው ገንዘብ መጠን 385 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር እንደደረሰ ይህም በ2007 አ.ም. ከነበረው በ115 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር እንደጨመረ ተገለፀ፡፡ በዚህ ከፍተኛ እምርታ ውስጥ ከአፍሪካ ወደ እንግሊዝ አገር ባንኮች ከገባው ውስጥ ከካሜሮን የወጣው ገንዘብ በቀዳሚነት በ516 በመቶ የጨመረ ሲሆን በሁለተኛነት ከኢትዮጵያ የወጣው በ103 ከመቶ መጨመሩን አንድሩ ሲምስ የተባለው አዲሱ የኢኮኖሚ ተቁዋም (The New Economics Foundation) የፖሊሲ ዳይሬክተር አስታወቁ፡፡ በተለያየ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ከሚገኙት ከእነኝህ ድሀ አገሮች እንደዚህ አይነት ከፍተኛ ሀብት መሸሹ በነኝህ አገሮች ውስጥ በአደገኛ ሙስናና ጤናማ ባልሆነ መንገድ የተመዘበረ የህዝብ ገንዘብን ጤናማ የማስመሰል እጥበት (money laundering) እየተካሄደ መሆኑን የሚያመለክት፤ በጣም ዘላቂ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትል አደገኛ ሁኔታ እንደሆነ አንድሩ ሲምስ አስምረውበታል፡፡

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ በሃገራችን የአምባገነንት እድሜ እንዲራዘም የሚፈጽመውን ደባ ሊያቆም ይገባዋል

በምርጫ 97 ህዝብ ተጠቦና ተጨንቆ የሰጠውን ድምጽ መለስ ዜናዊ ኮሮጆ እየገለበጠ ዘረፈው፡፡ ዝርፊያው ይቁም፣ የህዝብ ድምጽ ይከበር ያለውን ዜጋ አረደው፣ አሳደደው፣ ወህኒ አጎረው፡፡ እንዲህ አይነቱ የመለስ ዜናዊ እብሪት የኢትዮጵያን ህዝብ ቢያበግነውም መለስ አምባገነን መሆኑን አስቀድሞ ህዝብ ያውቅ ነበርና በመለስ ድርጊት ግራ አልተጋባም፡፡

የኢትጵያን ህዝብ ያስገረሙት ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ቆመዋል ብሎ ያምንባቸው የነበሩ የምእራብ መንግስታት፣ በተለይ በቡሽ ሲመራ የነበረው የአሜሪካ አስተዳደር በወቅቱ የኢትዮጵያን ህዝብ በገሃድ የታየ የዴሞክራሲና የነጻነት ፍላጎት አይቶ እንዳላየ በመሆን ዴሞክራሲና ነጻነት ረጋጭ ከሆነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጎን መቆሙ ነው፡፡ ለእዚህ አሳፈሪ ሚና ተጠያቂዎቹ ከቡሽ አስተዳደር ጭፍንና ጊዜያዊ ፍላጎትን ብቻ ያሰላው ፖሊሲ በአንድ በኩልና በቀድሞው ፕሬዚደንት በቡሽ አስተዳደር ውስጥ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የአፍሪካ ጉዳይ ክፍልና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ባለስልጣናት በሌላ በኩል ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ የአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በምርጫ ከደረሰበት ሽንፈት እንዲያገግም ለማድርግ ሲል በኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ፍላጎት ላይ ያልፈጸመው በደል የለም፡፡ መለስ ዜናዊ ምርጫውን ማጭበረበሩና ከእዚህም ጋር ተያይዞ እየወሰደ የነበረው አምባገነናዊ እርምጃ ያሳሰባቸው የአውሮፓ መንግስታት በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ጠንካራ አቋምና እርምጃ እንዳይወስዱ በአዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ የቡሽ አስተዳደር መለስ ዜናዊን በመደገፍ የራሱን የተናጠል እርምጃ እንዲወስድ በማድረግ የተጫወተው አፍራሽ ሚና ይታወቃል፡፡ የቡሽ አስተዳደር የደገፈውን የመለስን ግፈኛና ህገ-ወጥ አገዛዝ አውሮፓውያኑ በመቃወም የሚያመጡት ፋይዳ እንደማይኖር በመረዳታቸው አቋማቸውን አስተካክለው በመለስ አገዛዝ ላይ ሊወስዱ አስበውት የነበረውን ጠንካራ የተቃውሞ አቋም ማስተካከል እንደተገደዱ ከአውሮፓ ባለስልጣናት የሰማነው ሃቅ ነው፡፡

የቡሽ አስተዳር የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፣ በኤምባሲው በኩል በሚደርሰው መረጃ ላይ በመመስረት፣ መለስ ምርጫውን ካጭበረበረ፣ ህዝብን በገፍ ካረደና ካጋዘ በኋላ ለመለስ የግፍ አገዛዝ የገንዘብና የመሳሪያ ድጋፍ፣ በስለላና በአፈና የላቀ ስልጠናና ትብብር ያደረገበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህንን ታሪክ የማይረሳውን፣የኢትዮጵያን ህዝብ የነጻነትና የዴሞክራሲ ጥማትና ፍላጎት በማሰናከል በአሜሪካ ውጭው ጉዳይ ሚነስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ በአፍሪካ ጉዳይ ስልጣን የነበራቸው ጀንዳይ ፍሬዘርና በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ አምባሳደር በመሆን የሚያገለግሉት አምባሳደር ያማሞቶ የፈጸሙትን በደል ሳንጠቅሰው አናልፍም፡፡

በተለያዩ አጋጣሚዎች በአሜሪካን ምክር ቤት የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አማካይነት በሚዘጋጁ ልዩ ሰብሰባዎች ላይ በመገኘት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የፈጸመውን ከፍተኛ ወንጀል በመሸፋፍን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋ የሚሰጥ የፖለቲካ ሁኔታ እንዳለ በመግለጽ በተደጋገሚ የመለስን አገዛዝ በበጎ እየሳሉ የምክር ቤቱን የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ጸረ መለስ ዜናዊ ጠንካራ አቋም ለመሸርሸር፣ ኮሚቴው በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ አሳስቦት ያዘጋጃቸውን የነጻነትና የሰብአዊ መብት ጥበቃ የሚመለከቱ የህግ ረቂቆች ህግ ሆነው እንዳይወጡ ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም የኤሜሪካን ኤምባሲ ሃላፊነት ለአምባሳደር ያማሞቶ ከመተላለፉ በፊት የኤምባሲው ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩት ወይዘሮ ቪኪ ሀድልስተን በሃገራችን ፖለቲካ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት፣ ወያኔ ቅንጅትን ለመከፋፈል የሚያደርገው ጥረት አካል በመሆን ለመንቀሳቀስ በቅተው እንደነበር ይታወቃል፡፡ የቅንጅት መሪዎች እስር በነበሩበት ወቅት ለእስር ያልተዳረጉ የቅንጅት መሪዎችንና አባለትን እየሰበሰቡ ድርጅቱ የወሰደውን አፈሲያሊያዊ አቋም ተጻረው ፓርላማ እንዲገቡ፣ የአዲስ አበባን አስተዳር እንዲረከቡ፣ የቅንጅትን አመራሮች አስር ቤት ትተው የራሳቸውን መሪዎች መርጠው ቅንጅት ነን ብለው እንዲንቀሳቀሱ ወይዘሮ ቪኪ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም፡፡ ልደቱ አያሌውን የመሰለ ከሃዲ በማስተናገድና በቅንጅት ላይ ለፈጸመው ደባ ያልተቋረጠ ድጋፋቸውን መስጠታቸው በምሬት ህዝብ የሚያስታውሰው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ አልበቃ ብሏቸው ቃሊቲ ድረስ በመሄድ የታሰሩት የቅንጅት መሪዎች ለእዚህ ተግባራቸው ቡራኪያቸውን እንዲሰጧቸው በድፍረት ጥያቄ እስከማቅረብ ደርሰው እንደነበር ይታወቃል፡፡

ይህ የኤምባሲው አፍራሽ ሚና ወይዘሮ ቪኪ ተነስተው አምባሳደር ያማሞቶ ከተተኩ በኋላም አላቆመም፡፡ ሽብርተኛነትና የአካባቢን አለመረጋጋት ከሚያባብሱት ምክንያቶች አንዱ የዴሞክራሲ መጥፋትና መለስን የመሰሉ አምባገነኖች መግነን መሆኑ እየታወቀ የቡሽ አስተዳደር በጸረ ሽብር አጋርነት ስም ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያልተቋረጠ ድጋፍ እንዲያደርግ አምባሳደር ያማሞቶና በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ በአፍሪካ ጉዳይ የተመደቡት የስራ ባለደረቦቻቸው ተግተው ሰርተዋል፡፡ ከእዚህ በተጨማሪ አምባሳደር ያማሞቶ ከተሾሙ በኋላ በአሜሪካን ኤምባሲ ተቃዋሚዎችን በየግዜው በመሰብሰብ የሚያደርጓቸው ውይይቶች የሚጠቁመው አምባሳደሩ ጭንቀታቸው በቡሽ አስተዳደር የተሳሳተ ፖሊሲ የተነሳ ከፍተኛ ድጋፍ ሲሰጠው የቆየው የወዳጃቸው የአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ መንግስት፣ የህዝብ ድመጽ ዘርፎ ህዝብ ጨፍጭፎ የያዘውን ህገ-ወጥ ስልጣን በሌላ ዴሞክራሲያዊ በሚመስል ምርጫ ህጋዊነት ማላበስና ስንደግፈው የነበረው መንግስት ይኸው በህዝብ ተመረጠ ለማለት የታቀደ ይመስላል፡፡

ከእዚህ በፊት የግንቦት 7 ድምጽ ጋዜጣ አምባሳደር ያማሞቶ ከተቃዋሚ ደርጅቶች ጋር የሚያደርጉት ስብሳባ ተቃወሚዎች በ2002፣ መለስ የሚያደርገውን የይስሙላ ምርጫ አንሳተፍም እንዳይሉ ማባበል፣ የድጋፍ ቃል ኪዳን መግባት መሆኑን ለንባብ አብቅቶ ነበር፡፡ አምባሳደሩ በአንድ ስብሳባ ላይ ከ 2002 ምርጫ በፊት ከቦታቸው እንደማይነሱና ምርጫው እስከሚጠናቀቅ እንደሚኖሩ ያላቸውን ተስፋ ለተቃዋሚወች በማሳወቅ ተቃወሚዎች ተደፋፍረው ለምርጫ እንዲዘጋጁ የሚያደርግ መልእክት ማስተላለፋቸውን መግለጻችን ይታወሳል፡፡ሰሞኑም ከተቃዋሚዎች ጋር ያደረጉት ውይይት የሚጠቁመው ነገር ቢኖር አሁንም አምባሳደሩ ተቃዋሚዎች በ2002 ምርጫ እንዲሳተፉ የሚጎተጉቱ መሆናቸውን ነው፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ፣ በሃገራችን ምርጫ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችል ትንሽም ቢሆን የዴሞክራሲ ሁኔታ ቢኖር በአምባሳደር ያማሞቶ ጉትጎታ ባልተገረመ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ግን ፈጽሞ የለም፡፡ በ1997 መለስ ዜናዊ የእራሱን ዝናና ክብር ለማግነን ሲል ከፍቶት የነበረው የዴሞክራሲ ጭላንጭል ተዳፍኗል፡፡ የህዝብን መብት ማስከበርና የዴሞክራሲ ምርጫ ተገን መሆን የሚችሉ ነጻና ገለልተኛ ተቋማት በሃገራችን የሉም፡፡ በምርጫ ስም ህዝብ ላይ የተፈጸመው ግፍና እልቂት ከህዝባችን ህሊና ውስጥ ይተራመሳል፡፡ ታዲያ እነዚህ ለነጻና ለፍትሃዊ ምርጫ መኖር፣ ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሂደት መጠናከር ቁልፍ የሆኑ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ የአምባሳደር ያማሞቶን «ለሚቀጥለው ምርጫ ተሳተፉ፣ ተቃዋሚዎች ተሰባሰቡና አንድ ሁኑ፣ አንድ ከሆናችሁ እኛ ልንረዳችሁ አንችለላን» የሚለውን የሰሞኑን ውትወታ ምን አመጣው?

ግንቦት7 ይህ የአምባሳደሩ የሰሞኑ ውትወታ አልሞት ያለው የወደቀው የቡሽ አስተዳደር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቅሪት ነው የሚል እምነት አለው፡፡ አዲሱ የአሜሪካ አስተዳደር የውጭ ፖሊሲውን በአፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር ከሰው ልጆች ነጻነትና መብት መከበር ጋር በማቆራኘት የአሜሪካንን የተበላሸ ምስል ለማደስ በሚጥርበት፣ የአለም ህዝብም ይህ ፖሊሲ በተግባር ይውላል ብሎ በተስፋ በሚጠብቅበት ወቅት አማባሳደር ያማሞቶ አንዴ ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ስሜት የመለስ ዜናዊን መንግስት በይስሙላ ምርጫ የህጋዊነት ልባስ ለማላበስ የሚያደርጉት ጥረት ግንቦት ሰባትን የሚያሳዝነው፣ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያስቆጣው እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል፡፡ ባይሆን የአዲሱን የአሜሪካ አስተዳደር አዲስ ራእይ ተላብሶ በኢትዮጵያ እውነታኛና ነጻ ምርጫ እንዲደረግ በቅድሚያ የነጻ ሚድያ፣ የገለልተኛ የፍትህ ተቋም፣ በነጻ የተደራጀ የመከላከያና የደህንንት ሃይል አስፈላጊነትን በመጠቀም መለስ ዜናዊ ስለምርጫ ከማውራቱ በፊት ከተቃዋሚዎች ጋር በእነዚህ ተቋማት ምስረታ ዙሪያ ድርድር እንዲገባ ተጽእኖ ማደርግ በተገባ ነበር፡፡ ካልሆነም አርፎ ይቀመጧል፡፡ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሊኖር እንደማይችል ህጻናት እንኳን በሚያውቁበት ሃገር ተቃዋሚዎችን ሰብሰቦ ለምርጫ ተዘጋጁን ምን አመጣው? አምባሳደር ያማሞቶ ከእዚህ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ፤ ለራሳቸውና ለሕዝባቸው የሚፈልጉትን የነፃነትና የዴሞክራሲ ስርአት በኢትዮጵያችን ላይ ለማስፈን ባይደክሙ እንኳዋን ቢያንስ አይን ላወጣ አምባገነንነት ወዳጅ እንዳይሆኑ የግንቦት 7 ንቅናቄ ይማጸናል፡፡ የኦባማ አስተዳደርም የቡሽ አስተዳደር በኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ፍላጎት ላይ ከፈጸመው መሰረታዊ ጥፋት ተምሮ የሃገራችን ህዝብ ለነጻትና ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል ደጋፊ እንዲሆን ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ለጥሪውም አዎንታዊ ምላሽ እንደሚያገኝ የግንቦት7 ንቅናቄ ጽኑ ተስፋ አለው፡፡

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org

# ሃይለ ሀሳብ

## መለስ ዜናዊና የቁጩ ፓርላማው

### ከአዲስ አበባ

ይህንን አጭር መጣጥፍ እንድጽፍ ያስገደደኝ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን በፓርለማ ውስጥ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው በእብሪት የተሞላ መልስ ነው፡፡ ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ከሁሉም ጥያቄዎች መለስ በሱማሊያ ስለሞቱት ወታደሮቹ ቁጥር ሲጠየቅ የሰጠው መልስ ነው ብእሬን በምህላ ካስቀመጥኩበት እንዳነሳ ያደረገኝ፡፡ ጣቴን ለሌላ ነገር እንጅ በመለስ ላይ ብእር አላነሳበትም ብዬ ከስቀመጡት ብዙ ግዜ ሆኖኝ ነበር፡፡

መለስ ዜናዊ «የሞቱትን ማወቅ ለስራችሁ የሚያስፈልጋችሁ አይደለም፡፡ እኔም ብሆን ለእናንተ የመንገር ግዴታ የለብኝም» ብሎ ሲናገር ሰምቼ አላስችል አለኝ፡፡ እንዲያው ይህ በእብሪት የተሞላ ምላሹ እንድገነፍል አደረገኝ እንጂ ብእርህን አንሳ እያሉ ሲገፋፉኝ የነበሩ ስሜቶቼ ብዙ ናቸው፡፡ የመለስ ዜናዊ ፓርላማ የቁጩ ፓርላማ ስለሆነ ተቃዋሚዎች በተሰጣቸው ግዜ መለስ ዜናዊ ይጠይቃሉ እንጂ እሱ ለጥያቂያቸው በሰጠው ምላሽ ላይ መለሰው የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ እርሱ ባለተጠየቀበት ጉዳይ እንዳሻው ሲናገርም ተቃዋሚዎቹ ጥየቄ ማንሳት አይችሉም፡፡

ይህ የፓርላማ ስርአት የተደራጀው መለስን በጥያቄ የሚያፋጥጡ ደፋር የምክር ቤት አባላት ቢገኙ የመለስ ውሸታምነትና ደንቁርና በ1997ቱ የምርጫ ውድድር ከተቃዋሚዎች ጋር ለክርክር ቀርበው እንደተጋለጡት ጀሌ ካድሬዎቹ እንዳይጋለጥ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ በሌላ በኩልም ተቃዋሚዎች የምክር ቤቱን መድረክ በመጠቀም ህዘብ በነጻነት ማግኘት የማይችለውን በሃገርና በህዝብ ላይ የሚሰራ በደል ማቅረብ እንዳይችሉ ታሰቦ ነው፡፡ ይህ አሰራር የፕሮፓጋንዳ ሜዳውን ሙሉ በሙሉ ወያኔ በሬ ወለደ የሚለውን ውሸቱን ለማሰራጨት እንዲችል አመቻችቶለታል፡፡

በሱማሊያ ስለሞቱት ወታደሮች መለስ የሰጠው መለስ ያሳሰበኝ ነገር ቢኖር የወያኔንነ ፕሮፓጋንዳ በንቀት ማለፍ እንደሌለብን፣ እኔም ብእሬን በመለስ ላይ አለናሳም የልኩት ተገቢ እንዳልሆነ ነው፡፡

እንዲያውም ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው የሚባለውን የአበው አበባል ላሰበው የወያኔን የሃሰት ወሬና ቱልቱላ እየተከታቱሉ እርቃኑን ማስቀረት፣ የወያኔን የሃሰት ማስረጃ በእውነተኛው መረጃ ውሸት መሆኑን ህዝብ እንዲውቅ ማድረግ ችላ ልንለው የማይገባ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ይህችን የዛሬዋን መልእክቴን የግንቦት ሰባት ደምጽ ሬድዮ ከወደደለኝ በሌሎችም ገዳዮች ላይም ፓርለማውን ማእከል ያደረጉ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ጽሁፎችን ለማቅረብ አሞክራለሁ፡፡

አቀራረቤ የአራት ኪሎው የመለስ ፓርማ እውነተኛ ፓርላማ ቢሆን በተለያዩ ጉዳዮች በእዚህ ፓርላማ ውስጥ የሚደረጉ ወይይቶች ምን ይመስሉ እንደነበር የሚያሳይ ይሆናል፡፡ የዛሬው ትኩረቴ የሱማሊያ ወረራ ጉዳይ ነው፡፡

ተቃዋሚዎች መረጃ አሰባስበው የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ምን እንደሚመስሉ ምክር ቤቱ የዴሞክራሲ ፍንጭ የሚታይበት ቢሆን ኖሮ በመለስና በደፈር የምክር ቤት አበላት መሃል መካሄድ ይችል የነበረው ውይይት፣ ጥጣቄና መለስ ምን ሊመስል ይችል እንደነበር እንደሚከትለው አቀርባለሁ፡፡

ከሱማሊያ ወረራ በኋላ በተገኘው መረጃ መለስ ለፓርላማው ወታደሮችን ስለማለክ አጀንዳ አስይዞ ፓረለማው በሱማሊያ ጣልቃ እንድንገባ ይወስን ሲል በሽዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቹን አስቀድሞ አስገብቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ለፓርላማ ውሳኔ ለማቅረብ ሲዘጋጅ ደግሞ ቀድሞ ለአመታት ሶማሊያ ውስጥ ገብተው ሲነቃነቁ በነሩት ወታደሮቹ ላይ በሁሉም መልኩ የተደራጀ ጦር አስቀድሞ አሰገብቶ ነበር የነበረውን ጦር አሳድጎ ነበር፡፡ ይህ ዛሬ ጸሃይ የሞቀው ሃቅ ነው፡፡

እንግዲህ በጤነኛና በነጻ ፓርላማ መጠየቅ የሚገባው ጉዳይ መለስ ዜናዊ ፓርለማ ሳይወስን አንድን ልኡዋላዊ ሃገር በስልጣኑ እንዴት መውረር እንደቻለ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ታላቅና መሰረታዊ ከሃገር ደህንነት ጋር የተያያዘ ጉዳይ በመሆኑ ጤነኛና ነጻ ምክር ቤት ባለበት ሃገር ውሳኔው የሚሆነው ፓርላማው፣ ጠቅላይ ሚኒሰትሩን ከሰልጣኑ አንስቶ በሀገር ክህደት ክስ ተከሶ ለፍርድ እንዲያቀርብ ማድረግ ነበር፡፡ መለስ ያለፓርላማ ውሳኔ ሶማሊያን መውረር ብቻ ሳይሆን ለመውረር በሰጣቸው የሃሰት ምክንያቶች ሊጠየቅ ይገባ ነበር፡፡

መለስ ለምክር ቤቱ ሳያቀርብ በሽዎች የሚቆጠሩ ሰራዊቶቹን ሱማሌ በማስገባት ባከሄደው ወረራ የተቆጩ የሱማሊያ ታጣቂዎች ከሃገራችን ካልወጣህ ጀሃድ ቢትዮጵያ ላይ እናውጃለን ሲሉት፣ የሱማሊያ ታጣቂዎች ሳንደርስባቸው ጀሃድ አወጁብን ልማታችንን ሊያደናቅፉ ብሄራዊ ደህንነታችንን የሚገዳ እርምጃ ለፈጽሙ እየተዘጋጁ ስለሆነ እንምታቸው የሚል ሃሰት ለፓረለማው አቅርቧል፡፡ ይህ ደግሞ ፓርለማን በማሳሳት የሚያስከስስ ሌላ አብይ ወንጀል መሆን ነበረበት፡፡

ሱማሊያ ውስጥ በመግባት በሶማሊያ ህጻናት አረጋውያን ላይ የፈጸመው ግፍ የአለም የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በሚያንጫጫበት ወቅት፣ በሃገራችን እውነተኛ ፓርላማ ቢኖር የእነዚህን የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በመረጃ የተደገፈ ሰነድ ተቃዋሚዎች በማቅረብ፣ እንዴት እንዲህ አይነቱ ወንጀል በሃገራችን ስም ሊፈጸም እንደተቻለ በእዙህ የወንጀል ስራ መለስን ሊጠይቁት ይችሉ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ በሚገባ ተጣርቶ እውነት ከሆነ መለስ ዜናዊ በሰው ልጆች ላይ በፈጸመው የጦር ወንጀል በሃገሩ ፍርድ ቤት ይጠየቅ ነበር፡፡ ወይም ጉዳዩን የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲያው ምክር ቤቱ ሁኔታውን የሚያመቻች ውሳኔ ያሳልፍ ነበር፡፡ ስለ ሃገራችን ፍረድ ቤት የጠቀስኩት አሁን ያለውን እንደ ምክር ቤቱ የተኮላሸውን ፍርድ ቤት ከቁም ነገር ቆጥሬ አይደለም፡፡ እውነተኛ ፓርላማ ባለበት ሃገር የፍትህ ስርአቱም ነጻና ገለልተኛ ይሆናል ዳኞችም በሆዳቸው ሳይሆን በህሊናቸው የሚፈርዱበት ሁኔታ ይኖራል በሚል ስሌት አድርጌ ነው፡፡

ከሰልጣኑ አንስቶ በሀገር ክህደት ክስ ተከሶ ለፍርድ እንዲያቀርብ ማድረግ ነበር፡፡ መለስ ያለፓርላማ ውሳኔ ሶማሊያን መውረር ብቻ ሳይሆን ለመውረር በሰጣቸው የሃሰት ምክንያቶች ሊጠየቅ ይገባ ነበር፡፡

መለስ ለምክር ቤቱ ሳያቀርብ በሽዎች የሚቆጠሩ ሰራዊቶቹን ሱማሌ በማስገባት ባከሄደው ወረራ የተቆጩ የሱማሊያ ታጣቂዎች ከሃገራችን ካልወጣህ ጀሃድ ቢትዮጵያ ላይ እናውጃለን ሲሉት፣ የሱማሊያ ታጣቂዎች ሳንደርስባቸው ጀሃድ አወጁብን ልማታችንን ሊያደናቅፉ ብሄራዊ ደህንነታችንን የሚገዳ እርምጃ ለፈጽሙ እየተዘጋጁ ስለሆነ እንምታቸው የሚል ሃሰት ለፓረለማው አቅርቧል፡፡ ይህ ደግሞ ፓርለማን በማሳሳት የሚያስከስስ ሌላ አብይ ወንጀል መሆን ነበረበት፡፡

ሱማሊያ ውስጥ በመግባት በሶማሊያ ህጻናት አረጋውያን ላይ የፈጸመው ግፍ የአለም የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በሚያንጫጫበት ወቅት፣ በሃገራችን እውነተኛ ፓርላማ ቢኖር የእነዚህን የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በመረጃ የተደገፈ ሰነድ ተቃዋሚዎች በማቅረብ፣ እንዴት እንዲህ አይነቱ ወንጀል በሃገራችን ስም ሊፈጸም እንደተቻለ በእዙህ የወንጀል ስራ መለስን ሊጠይቁት ይችሉ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ በሚገባ ተጣርቶ እውነት ከሆነ መለስ ዜናዊ በሰው ልጆች ላይ በፈጸመው የጦር ወንጀል በሃገሩ ፍርድ ቤት ይጠየቅ ነበር፡፡ ወይም ጉዳዩን የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲያው ምክር ቤቱ ሁኔታውን የሚያመቻች ውሳኔ ያሳልፍ ነበር፡፡ ስለ ሃገራችን ፍረድ ቤት የጠቀስኩት አሁን ያለውን እንደ ምክር ቤቱ የተኮላሸውን ፍርድ ቤት ከቁም ነገር ቆጥሬ አይደለም፡፡ እውነተኛ ፓርላማ ባለበት ሃገር የፍትህ ስርአቱም ነጻና ገለልተኛ ይሆናል ዳኞችም በሆዳቸው ሳይሆን በህሊናቸው የሚፈርዱበት ሁኔታ ይኖራል በሚል ስሌት አድርጌ ነው፡፡

እንግዲህ ይህንን ሁሉ የተጣያቂነት ካፍተኛ ጉዳዮች መለስ በተአምር ካለፈ፣ ነጻ የሆነ ምክር ቤት በሱማሊያ ወረራ ሃገራችን ያተረፈችው ምንድነው የሚል ጥያ ቄ በማንሳት መለስን መጠየቅ ይችል ነበር፡፡ የመለስ ምላሽ እንደተለመደው አሸባሪዎችን አከረካሪያቸውን መትተናል፣ ከኤርትራና መንገስት ድጋፍ የሚያገኑትን የሶማሊያ አንጃዎች ሌሎች የሃራችንን ታጣቂዎች አውድመናል የሚል ከሆነ ሌላ ጥያቄ አከታትሎ ሊቀርብለት የሚገባ ይሆን ነበር፡፡

ይህም «ከሶማሊያ መንግሰትና ከሚደግፈው የመለስ ዜናዊ ጦር ጋር ተዋግቶ እንህ ሁለት ሃይሎች በጋራ ይዘውት ከነበሩት ከተሞች በሙሉ አባሮ ባድዋ ላይ ተንጥልጥለው እንዲቀሩ ያደረገው በአልሸባብ የሚመራው አክራሪ አንጃ መሆኑ እየታወቀ፣ እንዲያውም መለስ ሶማሊያን ሲወር አብዛኛው ግዛት ተቆጣጥሮ የነበረውን የእስልና ፍረድቤቶች አስተዳደር በማፍረስ ለአክራሪዎቹ ሁኔታዎቸን ያመቻቸው መለስ ዜናዊ መሆኑ እየተዋቀ መለስ አይኑን በጨው ታጥቦ «ድልን ተቀዳጅተናል፡፡ ያገራችን ብሄራዊ ደህንነት የሚየስከብር ስራ ሰርተናል» የሚል ሃሰት ሲያሰራጭ አንድ ነጻ ምክር ቤት ዝም ብሎ አይለቀውም ነበር፡፡ እንዲያውም በሱማሊያ ወረራ ሰራዊቱ በሽንፈት እንዲወጣ በማድረግ ሃገራችንን ለመድፈር ለሚፈልጉ ሁሉ ታለቅ የሞራል ማነሻሻ የሰጠ፣ በወረራው በተፈጸመው ግፍ ኢትዮጵያን አምረው የሚጠሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሱማሌዎችና በሌሎች ቦታዎች የሚገኑ ደጋፊዎቻቸውን ያበረታታ መሆኑን በግለጽ ማስቀመጥ ይቻል ነበር፡፡ መለስ ዜናዊም የሃገራችን ክብር በማዋረድ፣ መግባት በማይገባት ወረራ ውስጥ ገብታ እንድትሸነፍ በማድረግ፣ ከፍተኛ የሃገረ ነዋይና የዜጎቿ ህይወት እንዲወድም በማድረግ ሌላ ሃገር ክህደት ክስ ሊመሰረትበት የሚያስችል ነበር፡፡

በተመሳሳይ በቅርቡ በፓርለማው ውስጥ ለቀረበለት ጥያቄ መለስ ምላሽ ለመስጠት አልገደደም ብሎ ሲዝናና፣ የመናገር መብት ያላቸው የፓርለማ ተወካዮች ሉበት ሁኔታ ቢኖር ጥያቄውን አዞረው እንዲህ ብለው ሊጠይቁት ይችሉ ነበር፡፡

«ጠቅላይ ሚስቴር

በእጃችን የገባው መረጃ እንደሚያሳየን በሱማሌ ወረራ የሞተውና በከባዱ የቆሰለው 3027 ወታደር ሲሆን ከእዚህ ውስጥ የሞተው 1426 ሲሆን በጽኑ የቆሰለው 1601፡፡ ከሞቱት መሃል 3 ወታደሮች በእሳት እየጋየ እሬሳቸው የተጎተተ ሲሆን፣ አንገታቸው ተቆርጦ የታጣሉ 23 ወታደሮች ይገኙበታል፡፡ ከእዚህ በተጨማሪ ወደ ሱማሊያ ከተላኩት ወታደሮች መሃል 1007 በጠቅላላው የት እንደደረሱ የማይታወቅ ነው፡፡ በግምት ግን ከእነዚህ መሃል የተማረኩ፣ የሱማሊያን ታጣቂዎች የተቀላቀሉ፣ መሳሪያቸውን ለጠላት አስረክበው ወደ የመን የተሰደዱ እንዳሉ የሚያሳይ መረጃ በቢሮ እንደሚገኝ እናውቃለን፡፡ ለምድ ነው ይህንን መረጃ ለምክር ቤት ማቅረብ የማይደፍሩት የሚል ጥያቄ መቅረብ በቻለ ነበር፡፡

መለስ አልመልስም ያለው ጥያቄ፣ የሶማሊያ ወረራ በሃገራችን ደህንነት፣ በሃገሪቱ የተራቆተ ሃበት ላይ ያስከተለው ኪሳራ ብቻ ሳይሆን፣ የሃራችን ዜጎች በተለይ ለመኖር ሲሉ አማራጭ አጥተው በወታደርንት የተቀጠሩ የደሃ ዜጎቿ ህይወት ላይ ቁማር የተጫወተበት መሆኑን ስሚያውቅ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰት አሃዞች መጠን የኢትዮፕያውያን ነፍስ መርገፉን ምክር ቤቱም ሆነ ህዝብ እንዲያውቀው ስለማይፈልግ ነው፡፡ ምክንያቱም ሃገራችን ደህይታና ተዋርዳ ለወጣችበት ወረራ ይህንን ያህል የሰው ህይወት ማለፉ ሌላው በወንጀል የሚየስጠይቅ ጉዳይ ነውና፡፡ መለስ አልመልስም ላለው ጥያቄ መልሱ ይሀ ነው፡፡ ከሞቱት 1426 ወታደሮች ውስጥ 7 እህቶቻችን ይገኙበታል፡፡ በመረጃው ጦርነት ህዝብ ሲጠቃ ማየት ተገቢ አይደለምና የወያኔን ቅጥፍት ለማምከን የሚያስችሉ መረጃ ያላችሁ በሙሉ መረጃውን ለህዘብ አቅርቡ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡ የእዚህ መረጃ መውጣት ጦሱ እኔ ጋር እስካልደረሰ ድረስ።

**በሰላም ያገናኘን!**

## ሂውመን ራይትስ ዋች .......... (ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ የተያያዘውን አፈናና ዜጎችን የማሰቃየት ስራ ህጋዊ ለማድረግ የተጠነሰሰው ይህ አዋጅ፥ ፖሊስ ያለመጥሪያ ሰዎችን እና ቤት ንብረታቸውን በድንገት እንዲፈትሽ ስልጣን ከመስጠቱም በላይ፤ አንድ ፖሊስ በዚህ እጅግ በተዛባ ትርጉም ላይ ተመስርቶ አንድ የሽብርተኝነት ስራ ሊፈጸም ነው ብሎ ካሰበ የሰዎችን ንብረት የማውደም እና እንቅስቃሴ የመግታት ስልጣን ተሰጥቶታል።

በተጨማሪም፥ የደህንነት ሰዎች የዜጎችን የስልክ እና በሌላ መገናኛ መንገዶች የሚደረጉ ንግግሮች እንዲያዳምጡ ስልጣን የተሰጣቸው ሲሆን፥ አንድ ሰው በወንጀል ሳይከሰስ እስከ አራት ወራት በእስር ቤት እንዲቆይ የሚያደርግ ድንጋጌም ተካቷል። ይህም የኢትዮጵያን ህገ-መንግስትም ሆነ ዓለም አቀፍ ህጎችን እንደሚፃረር ሂውማን ራይትስ ዋች ገልጿል።

ማስረጃዎችን በተመለከተ፥ ረቂቅ አዋጁ አሉባልታ በፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው ከማስቻሉም በላይ፤ ሰዎችን በማሰቃየት የተገኘ ኑዛዜም እንደ ማስረጃ ተቆጥሮ ፍርድ ቤቶች እንዲቀበሉት ያደርጋል። ይህም የኢትዮጵያን ህገ-መግስትም ሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚጥስ ሲሆን፣ ቀድሞውኑ ወያኔ መሳለቂያ ያደረጋቸውን ፍርድ ቤቶች ወደ ባሰ የውርደት ቁልቁለት እንደሚወስድ ይገመታል።

በጣም አስገራሚ በሆነ ሁኔታ፥ በረቂቅ አዋጁ ከተጠቀሱት አንቀፆች አንዱ ዜጎች ስለ ሆነ ሽብር ተብዬ ስራ መረጃ ስላላቀረቡ ከሶስት እስከ አስር ዓመት በሚሆን እስራት እንደሚቀጡ የሚናገር ሲሆን፣ መልሶ ደግሞ ያቀረቡት መረጃ ሃሰት ሆኖ ከተገኘ ከሶስት እስከ አስር ዓመት እንደሚቀጡ ይናገራል። እንደ ሂውማን ራይትስ አገላለጽ ይህ ዜጎችን አስቸጋሪ በሆነ አጣብቂኝ ውስጥ ይጥላቸዋል።

የግንቦት 7 ዜና አቅራቢ ቀርቦ ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪ ስለዚህ ግራ አጋቢ አንቀጽ ሲናገሩ ወያኔ ይህንን የሚያደርገው ዜጎችን ሁሉ ሆን ብሎ ለመወንጀል እንደሆነ እና ያን ካደረገ በኋላ ባሰኘው ጊዜ ባሰኘው ሰው ላይ ህጉን እየመዘዘ ለመጠቀም እንደሚቀለው ተናግረዋል። "በዚህ ህግ አካሄድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሽብርተኛነት ወንጀል በመከሰሱ እና ባለመከሰሱ መሃል ያለው ክፍተት የወያኔ የዚያን ሰው መታሰር ወይም መገደል መፈለግ አለመፈለግ ነው" ብለዋል።

## ከመጠን ያለፈ የብድር .... (ከገጽ 1 የዞረ)

በሰኔ 2000 ዓ.ም የፌደራል መንግስት ተጠባባቂ ኦዲተር ጀነራል አቶ አሰፋ ደስታ፥ በ98 ዓ.ም አገዛዙ ህጉ ከሚፈቅድለት ውጪ 3.3 ቢሊዮን ብር ከብሔራዊ ባንክ መበደሩን ማጋለጣቸው የሚታወስ ሲሆን የገንዘብ ሚኒስቴር በወቅቱ መንግስት እያደረገ ስላለው ከፍተኛ ብድር ተጠይቆ ሲመልስ ከምርጫው በኋላ አንዳንድ የውጭ መንግስታት እርዳታ መቀነሳቸውን እንደ ምክንያት የጠቀሰ ቢሆንም፤ በኦዲተር ጀነራሉ ሪፖርት መሰረት ግን ብዙ የመንግስት ቢሮዎች ከበጀት በላይ ከማለፋቸውም ባሻገር ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ጠፍቶ ነበር። ኦዲተሩ፥ በዛ ዓመት ብቻ በህገ-ወጥ ግዢዎች እና ክፍያዎች፣ ከበጀት ውጪ በማድረግ እና ሌሎችም ምክንያታቸው ባልታወቀ ወጪዎች በድምሩ 2 ቢሊዮን ብር እንደጠፋ አጋልጠው ነበር። ለምሳሌ፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪፖርቱ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ከበጀቱ ውጪ 8.8 ሚሊዮን ብር ለኤምባሲዎች የተጠቀመ ሲሆን፣ በእጁ ደግሞ ተጨማሪ 34.9 ሚሊዮን ብር ይዞ ነበር። አገዛዙ፥ ከምርጫ 97 በኋላ ያደረሰውን ግፍ በመቃወም ሌት እና ቀን ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የእግር እሳት የሆኑበትን በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ለመቆጣጠር ለመሞከር ሰላዮችን ከመላክ አልፎ ብዙ ወጪ እንዳወጣ ይታወቃል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም በዛ ዓመት ያወጣው ተጨማሪ ወጪ ከዚህ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

በኦዲተር ጀነራሉ በቀረበው ሪፖርት ላይ በወቅቱ ጥያቄ የቀረበለት መለስ ዜናዊ፥ ምንም ስህተት እንዳልተሰራ በመዋሸት ነገሩን ለማስተባበል ከመሞከርም አልፎ፣ ተጠባባቂ ኦዲተር ጀነራሉን መዝለፉ እና እሱ በመረጠው ሰው መተካቱ ይታወሳል። በቅርቡ ግን፥ ያ ሁሉ ከመጠን ያለፈ ብድር የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከጎዳና ብዙ ኢትዮጵያውያን ከዋጋው ግሽበት የተነሳ ለመከራ ከተዳረጉ በኋላ፤ የውጭ ምንዛሪ ፍለጋ ለአለም አቀፍ ተቋማት ተማጽኖ ማድረግ የነበረበት መለስ፣ በብድር ላይ ቁጥጥር ለማድረግ መገደዱን መዘገባችን ይታወሳል።

'ኢትዮጵያን ኒውስ ኤንድ ቪውስ' በተባለ ድህረ ገጹ ላይ የአገዛዙን ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ በደል በማጋለጥ የሚታወቀው ዳግማዊ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ሲናገር፣ መለስ ዜናዊ አሁን ብድርን እንደሚቆጣጠር ለዓለም አቀፍ ተቋማት ቢናገርም ኦዲተር ጀነራሉን ይቅርታ አለመጠየቁንና ከ97 በኋላ ስለተከሰተው የዋጋ ግሽበትም ለኢትዮጵያ ህዝብ ገለፃ አለማድረጉን ኮንኗል። "ይህ የተለመደው መለስ ዜናዊ ነው - ጨቅላ፣ ሃላፊነት የጎደለው እና አንድም ቀን ስህተቱን የማያምን" ሲልም አስተያየቱን ደምድሟል።

## በበረከት ስምኦን በለንደን ......... (ከገጽ 1 የዞረ)

በፋሽስቱ በረከት ስምኦን ተጠርቶ የነበረው ይህ ስብሰባ ሊካሄድ ታስቦ የነበረው በለንደን በሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ ሲሆን ከወያኔ ጋር ባላቸው ቀረበታና የጥቅም ትሥስር ተለይቶ የተጋበዙትን ተሰብሳቢዎች ብቻ ለማስተናገድ እ ቅድ እ ንደነበረው የሰሙት ኢትዮጵያዊያን ቀደም ብለው ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት በቦታው በመገኘት ተጋባዦቻቸውን ለይተው ለማስገባት በተመደቡት የወያኔ ቅጥረኞችና በ ኢትዮጵያዊነታቸው ገብተው ስብሰባውን ለመከታተል መብት አለን በሚሉ ተቃዋሚዎች መካከል በተፈጠረው ጭቅጭቅ በወያኔ ሹሞች ላይ ከፍተኛ መደናገጥ እንደደረሰ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል ።

በሁነታው የተደናገጡት የ ኤምባሲው ሰረተኞች ችግሩ ከቁጥጥራቸው በላይ ሲሆንባቸው ለፖሊስ በመደወልና ከባድ ችግር ያለ በማስመሰል ልዩ የፖሊስ ሀይል እንዲመጣ ያደረጉ ሲሆን በስፍራው የተገኙት የፖሊች ሀይሎችም የችግሩን መንስኤ ከሁለቱም ወገን ከሰሙ ቦኋላ ስብሰባው በይፋ የተጠራና ኢትዮጵያዊያንን ለማሳተፍ ከሆነ ወደ መሰብሰቢያ ቦታ ከመጡት ውስጥ አንዱን ከሌላው ለይቶ አናሳትፍም ማለት በሰለጠነው ዓለም በአድሎነት እንደሚቆጠር በማስረዳት መግባባት እንዲፈጠር ከመጣር ውጭ እንደአጋዚ ጦር ተሰብሳቢውን በመሳሪያ የሚበትን ሊሆን ባለመቻሉ አንጀታቸው እንዳረረና ስብሰባቸውን ለመሰረዝ እንደተገደዱ ታውቆአል።

በረከት ስምኦን በስብሰባው ለመገኘት ሲመጣ የነበረው ግርግር ያስደነገጠውና መኪናውን የማይሆን ቦታ ላይ በማቆም ተደብቆ በሌላ በር እንዲገባ የተገደደ ሲሆን በጉዳዩ የተበሳጨትና ስብሰባው በሰላም እንዳሰቡት ያልሄደላችው አንድ የወያኔ ቡችላ በንዴት "ገሎም በጉልበት መኖር እኮ እውቀት ነው፤ ምን ታመጣላችሁ እያሉ" በፖሊሶች መሃል ሲንጎራደዱ እንደነበር ይህም ወያኔና የወያኔ ደጋፊዎች ያሉበትን የሞራል ውድቀት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ እንደሆነ በስፍራው የተገኘ ሁሉ ለማየት ችሎአል። ወያኔ ከቀን ወደቀን እየተባባሰ የመጣውን የህዝብ ቁጣ ለማብረድና የደረሰበትን የውጭ ምንዛሪ ኢጥረት ችግር ለመቅረፍ በውጭ አገር የጀመረውን የልመናና የልምምጥ ዘመቻ ለማክሸፍ እያንዳንዱ ቅን ኢትዮጵያዊ የዘግነት ግዴታ እንዳለበት የግንቦት 7 ድምጽ እያሳሰበ በፈረንጆች አቆጣጠር አፕርል 2 በለንደን በሚደረገው የሃያዎቹ ሃብታም አገሮች ስብሰባ ላይ ነፍሰገዳዩ መለስ ዜናዊ ሲለምሳተፍ ይህንኑ ለመቃወም በተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በአውሮጳ የሚኖር ማንኛውም አገር ወዳድ አንዲገኝ፡በአስተባባሪ ኮሚቴው ሥም ጥሪ ያስተላልፋል።

## በአፍሪካ ዝርፊያው ......... (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህን ጉዳይ በሰፊው የዘገበው ፊሊፕ ቶርንተን የተባለው የኢኮኖሚ ዘጋቢ እንዳመለከተው የዚህን የገንዘብ ሽሽት መጠን ለመረዳት እንግሊዝ በዚህን ጊዜ በአመት ለሁሉም ድሀ አገሮች ከምትሰጠው እርዳታ ጋር ማነፃፀሩ ይጠቅማል፡፡ እንደ ፊሊፕ ቶርንተን ዘገባ ከሆነ የእንግሊዝ ጠቅላላ የውጭ እርዳታ ባጀት በዚህን ጊዜ በአማካይ ወደ 6.4 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነው፡፡ ወደእንግሊዝ ባንኮች የሚገባው የድሀ አገሮች ገንዘብ ግን 385 ቢሊዩን ዶላር ነው፡፡ ስለዚህ በቅርብ አመታት ጨምሮአል የሚባለው የእንግሊዝ የውጭ እርዳታ እንግሊዝ ከነኝሁ ድሀ አገሮች ወደ ባንኮቹዋ ከሚገባው ገንዘብ ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ትንሽ መሆኑ ነው፡፡ የእንግሊዝ ኢኮኖሚ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሀ አገሮች የተሰበሰቡ ሽፍታ መንግስታትና አጫፋሪ ከበርቴዎቻቸው ከህዝባቸው በሚመዘብሩት ገንዘብ እየተደጎመ ነው ማለት ነው፡፡ ይህን ዜና አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጠን የጠየቅነው አንድ ኢትዮጵያዊ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ‹ነገሩን እጅግ አሳዛኝም አሳፋሪም የሚያደርገው ከዚህ ምስኪን ድሀ ሕዝብ የሚዘረፈው ገንዘብ ግዙፍነት ብቻ አይደለም፤ የዘራፊዎቹ አይን አውጣነትና ቅንጣት ታክል አገራዊ ስሜት የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ እስኪ ምናለ የዘረፉትን ገንዘብ እንኳዋን በአገራቸው ለማዋልና በረሀብ ለሚሰቃየው ህዝብ ስራ መፍጠሪያ ቢያውሉት? እንዴት አይን አውጣ ቢሆኑ ነው እነኝህ ሰዎች ይህን ያክል ገንዘብ ወደ ውጭ እያሸሹ መልሰው ሀብታም አገሮች ስብሰባ መጥተው የገንዘብ እርዳታ ስጡን ብለው የሚለምኑት? እንዴትስ ነው እነኝህ አገሮች ይህንን እያወቁ ለነኝህ ቀማኛ መንግስታት በሕዝቡ ስም ገንዘብ የሚሰጡዋቸው?› ነው ያለን፡፡

ይህ በአደገኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣው የገንዘብ ማሸሽ ሁኔታ በተለይ ለአገራችን በጣም አሳሳቢ የሚያደርገውና በርግጥም የሚያስገርመው ደግሞ ከዚህ በፊት በገንዘብ ማሸሽ ዙሪያ ስሟ ተነስቶ የማታውቀው አገራችን ከትላልቅ ገንዘብ አሻሽ አገሮች ተርታ መሰለፉዋ በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ተንሰራፍቶ የሚገኘው የዘረኛና የሽፍታ አገዛዝ ምን ያህል አደገኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጃንሆይ ገንዘብ አሸሹ ተብሎ ደርግ ሲያጣራ ተገኘ ከተባለው ጥቂት ሚሊዮን ዶላር አንፃር ሲታይ አሁን የሚካሄደው አይን ያወጣ የሽፍታ ዘረፋ በውነቱ በጣም የሚገርም ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ በአህጉራችን በሙስናና በምዝበራ ወደር አይገኝላትም እየተባለ እንደ ተአምር ይወራላት የነበረችውን ናይጄሪያን እንኳዋን እየቀደምን ነው፡፡ እንደ ፊሊፕ ኖርተን ዘገባ ከሆነ ባለፈው አመት የናይጄርያ ጉቦኛ የመንግስት ባለሟሎችና አጫፋሪ ባለሀብቶች ወደ እንግሊዝ አገር ባንኮች ያወጡት ገንዘብ በ47 ከመቶ ብቻ የጨመረ ሲሆን የኢትዮጵያው በ103 ከመቶ መጨመሩ በአገራችን እየተደረገ ያለው የአገር ሀብት ምዝበራ የደረሰበትን አደገኛ ደረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚያም አልፎ ግን የዚህ ዘረኛ መንግስት ዘራፊዎችና በሱ ከለላና ጠባቂነት የሚንቀሳቀሱት ባለሀብቶች ምን ያህል ተስፋ እየቆረጡ መሆኑንና መውደቂያቸው መቃረቡን አውቀው የዘረፉትን ገንዘብ ውጭ ሆነው ለመብላት እያሰፈሰፉ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት መሆኑን አንዳንድ ታዛቢዎች ይገልፃሉ፡፡

የእንግሊዝ መንግስት የዚህ ዝርፊያ ተባባሪ ካልሆነ ሊያደርግ የሚገባው በሕዝቡ ስም እርዳታ የሚሰጣቸው አገሮች ምንም የእርዳታ ገንዘብ ከማግኘታቸው በፊት በአገሩ ባንክ ውስጥ የተቀመጠው የየድሀ አገሮች ሰዎች ገንዘብ ምንያክል እንደሆነና ይህ ገንዘብ ደግሞ አስቀማጮቹ እነማን እንደሆኑ፤ በርግጥም ሰርተው ያገኙት ገንዘብ መሆኑን አለመሆኑን፤ በምን መልክ ገንዘቡም እንደወጣ አሳማኝና ግልፅ የሆነ መረጃ ለማህበረሰቡ ከተሰጠ በሁዋላ ሊሆን እንደሚገባው የአዲሱ የኢኮኖሚ ተቁዋም ዳይሬክተር አንድሩ ሲምስ አሳስበዋል፡፡

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።**

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።